ከ ኤፕሪልl 20, 2020 ጀምሮ MCPS የምግብ አገልግሎቶችን ፕሮግራም በሣምንት አምስት ቀን ከመሥራት ወደ አራት-ቀን-በሣምንት መርሃግብር ያስተካክላል። ይህ ማስተካከያ የሚደረግበት ምክንያት የተማሪዎችን እና የሠራተኞችን ጤንነት እና ደህንነት ለመጠበቅ፣ እና የኮሮናቫይረስ COVID-19 (coronavirus) ወረርሽኝ ስርጭትን ለመቀነስ ታስቦበት ነው። የምግብ አገልግሎት ጣቢያዎች ሰኞ፣ ማክሰኞ፣ እና አርብ በመደበኛ ሁኔታ ይሠራሉ። ረቡእ ቀን MCPS ለሁለት ቀኖች የሚሆን ምግብ ይሰጣል። ሐሙስ ቀን በጠቅላላ የምግብ አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ዝግ ይሆናሉ። የምግብ አገልግሎት የሚሰጠው ከ 11 a.m.–1 p.m. ነው። በተጨማሪ፣ MCPS ከ ኤፕሪል 22, 2020 ጀምሮ በየሣምንቱ እሮብ ቀን በህትመት የተዘጋጁ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን በምግብ ጣቢያዎች ይሰጣል። እነዚህ ማቴሪያሎች-ቁሳቁሶች ለኤለመንተሪ እና ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የሒሳብ እና የሊተርሲ ትምህርት- mathematics and literacy content ይሰጣሉ።

ልዩ ማስታወሻ፡- በዚህ ዓርብ ቀን ኤፕሪል 17፣ ቤተሰቦች ለቅድመ ምዋእለ ህፃናት እና ለኤለመተንተሪ ተማሪዎች በሁሉም የምግብ ጣቢያዎች 11 a.m.–1 p.m. ባለው ጊዜ ውስጥ የሒሳብ ጥራዞችን መውሰድ ይችላሉ። ኤፕሪል 17 ለመምጣት የማይችሉ ከሆነ፣ እሮብ ኤፕሪል 22 በተመሣሣይ ሠዓት ጥራዞቹን ለመውሰድ ይችላሉ።

More information

Maryland's Largest School District
**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**
*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

# ምግብ እና የማስተማሪያ ቁሳቁስ የሚከፋፈልበት የጊዜ ሠሌዳ

## ኤፕሪል 20/2020 ከሚውልበት ሣምንት ጀምሮ

MCPS ስለተማሪዎቻችን እና ሠራተኞቻችን ጤንነት እና ደህንነት ቁርጠኛ ነው። ከኤፕሪል 20/2020 ጀምሮ MCPS የምግብ ማከፋፈያ ጣቢያዎችን የጊዜ ሠሌዳ ያስተካክላል። ጣቢያዎቹ ሰኞ፣ ማክሰኞ፣ እና ዓርብ መደበኛ ሥራቸውን ይሠራሉ። ረቡእ MCPS ለሁለት ቀን የሚሆን ምግቦችን ይሰጣል። ሐሙስ ቀን፣ የምግብ መስጫ ጣቢያዎች በጠቅላላ ዝግ ይሆናሉ። ይህ ለውጥ የኮሮናቫይረስ ስርጭትን ለመቀነስ እና የምግብ ማዘጋጀት አቅማችንን ለመጨመር እድል ይሰጠናል። በተጨማሪ፣ ከኤፕሪል 22/2020 ጀምሮ ዘወትር ረቡዕ ቀን የታተሙ ማስተማሪያ ቁሳቁሶች በምግብ ማከፋፈያ ጣቢያዎች ላይ ይሠራጫል።

**ሰኞ**
- ቁርስ
- ምሳ
- እራት

**ማክሰኞ**
- ቁርስ
- ምሳ
- እራት

**ረቡእ**
- ቁርስ (x2)
- ምሳ (x2)
- እራት (x2)

- ሣምንታዊ የማስተማሪያ ቁሳቁስ ስርጭት

**ሐሙስ**

የመገናኘት እድሎችን ለመገደብ እና የምግብ ዝግጅትን ለመጨመር የምግብ ጣቢያዎች ዝግ ይሆናሉ

**ዓርብ**
- ቁርስ
- ምሳ
- እራት

- የሣምንት መገባደጃ የምግብ ከረጢቶች ከመና የምግብ ማእከል-Manna Food Center

የማከፋፈያ ጣቢያዎችን ዝርዝር እዚህ ማግኘት ይችላሉ :- MontgomerySchoolsMD.org/Coronavirus/Meals/#EmergencyMeals